


በነገድ ከፈሉት ተለየ አበሻ፣
ተጎሳቆለ አሉ ሕዝብ አጣ መድረሻ፤
አላስቀምጥ ቢለው ወያኔ ባገሩ
ሄደ ሞትን መርጦ ባኃር ገባ በእግሩ፤
ብዙ ነገር ሰማን ፍዳውን ውርደቱን
ቻይናውም አረቡም ያደረሱበትን፤
ባራቱ ማዕዘን ጩኸት በዛ ምነው
በአገር ልማት ሰበብ ዘር እየጠፋ ነው
ያሮሞ ያጋዴን ሁሉም በየተራ
በአፋር ስምጥ ሸለቆ ያሞና ጋምቤላ
በምድረ ኢትዮጵያ ታመሰ አሉ አማራ
ጸገዴ አርማጭሆ መተማ ሁመራ
ገበሬው ወልቃይት መነኩሴው ዋልድባ
ቤንሻንጉል ጉሙዝ ደቡብ ጉራፋርዳ
የግፍ እንባ ወርዶ ጽዋው የሞላ ዕለት፣
መድረሻውን እንጃ ወያኔ ወዮለት፡-
አገር ትጣራለች መከራው ጠንቶባት
የባንዳ ወያኔ የዘር ደዌ መቅሰፍት
የሞት ጣር ድምጽ በዛ ዝምታ ምንድነው
ክተት በል አበሻ ሕብረት ፈውሳችን ነው።

ጠላት የቀበረው የዘር መርዝ በስብሶ
በተናት ኢትዮጵያን በቋንቋ ቆራርሶ
የዘር ፖለቲካ ከሆነብን መርገም
ንቀሉት ከስሩ ለማንም አይበጅም፥
የደዌው መነሻ አድዋ ነው አሉኝ
ከዓሉላ አባነጋ ከዮሐንስ እልፍኝ
ትግሬ መላ ምታ አፋር እና ሐረር
ማርከሻ መዳህኒት ዓይጠፋም በጎንደር
ጊዜ እየጠበቀ ቢያገረሽበትም፤
እስካሁን አልቻለም አልተሳካለትም።
ወጌሻ ነው ጥሩት ምኒልክ ይቀስቀስ
ሰብሮ ይጠግነው ያባዳኘው ፈረስ
ተነስ አባ ታጠቅ መይሳው ቴዎድሮስ
ገብርዬን ላክልን የጦሩን መሃንዲስ
ከእንግሊዝ፣ ከድርቡሽ ከቱርክ ከጣሊያን
ጀግና አባቶቻችን ተፋልመው ያቆዩን
ሲባል የሰማሁት ጎጃም ጀግና ነበር
የበላይ ዘለቀ የሸፈራው አገር
ደጋ ቆላ ዳሞት ዱርቤቴና አቸፈር
ማርቆስ አልሰማም ወይ ዘጌና ባህርዳር።
አርሲና ባሌ፣ ከፋ ኢሊባቡር
ጋሞና ሲዳማ፣ ደቡብ የደጉ አገር
ጦር ጋሻህን ይዘህ እለፍ ወደ በሩ
አገር በቀል ጠላት ገብቷል በመንደሩ
ጎንደር ዝም አትበል ወለጋ ጭስ ታይቷል
የአንድነት እሳት ግለቱ ደርሶታል፥
ሚስቴ ተነሽ ውጭ አቀብይኝ ስንቄን
ልጀም ተከተለኝ አንሳ ዝናርህን፥
ሸዋ እንቢ በል ታጠቅ፣ ወሎም ተከተለን
ለአገር አንድነት እንዋደቅ አብረን፥